2013 ዓ/ም

# የሕግና ነቢያት ፍጻሜ

REVISED

በደረጀ አድሴ

ይህ ከቀድሞው የተራራው ስብከትና የሐዋርቱ ግልጠት ከሚለው
የሕግና ነቢያት ፍጻሜ በሚል ተሻሽሎ የቀረበ ነው።

Contact

+251967051982

Derejeofpad@gmailcom

# ይዘት

**1 ህግን መፈፀም 4**

እየሱስ የኃጢአት መስዋዕት

እየሱስ የሚቃጠል መስዋዕት

እየሱስ የደህንነት(የሰላም) መስዋት

እየሱስ የበደል መስዋዕት

እየሱስ የዕህል ቁርባን መስዋዕት

**2 የህግ መሻር 30**

ህጉ እንደጥላ ማገልገሉ

ህጉ እንደ ሞግዚት መገልገሉ

**3 ህግ ማድረግ 38**

# መግብያ

የአዲስ ኪዳን መጽሐፍት በአብዛኛው የሕግና ነቢያት ጥላ ወይም የትንቢት ፍጻሜ መጽሐፍት ናቸዉ።መጽሐፉም የብሉይ ኪዳን ፍጻሜ የሆነውም መጽሐፍቶቹ በቀጥታ ለእስራኤል ቢሆኑም መንፈስ መቅደስ በሚስጥር ለቤተክርስቲያን ስለተናገረ ነው። ስለዚህ በዚህች ትንሽ መጽሐፍ የምንመለከተው ጌታ ኢየሱስ በተራራው ስብከት ስለህግና ነብያት ካነሳው በመጀመር ይሆና ምክንያቱም በጣም ብዙ የታጨቀና ወሳኝ ስለሆነ፤ ብዙውን ጊዜ ደግሞ ሰዎች "ሕግና ነቢያት" ሚለውን ሀሳብ በማጥበብ ውስን ወደሆነ መረዳት ውስጥ ይገባሉ በተጨማሪም ደግሞ በእያንዳንዱ ርዕስ ውስጥ የምንመለከታቸው ድንቅ የአዲስ ኪዳን የመገለጥ እውነታዎችን እናያለን። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ህግን በተመለከተ ጌታ ኢየሱስ እና ሐዋርያት በተናገሩት ላይ አወዛጋቢ መስለው የሚታዩ ሶስት ነገሮች አሉ። እነሱም ፦ ህግን መፈጸም፣ህግን መሻር፣ ህግን ማድረግ ነው። እያንዳንዳቸውን በጥልቀት ከዚህ በመቀጠል እንመለከታቸዋለን።

# 1

# ህግን መፈጸም

በመጽሐፍ ቅዱስ ጌታ ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር በነበረበት ጊዜ በተለምዶ የተራራው ስብከት ተብሎ በሚጠራው ትምህርት ላይ ባስተማረው ላይ በተለይ ህግን መፈጸም በሚለው ሀሳብ እንጀምራለን። ማቴዎስ 5

**17እኔ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ልፈጽም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም።ኀ እውነት እላችኋለሁ፥ ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ፥ ከሕግ አንዲት የውጣ ወይም አንዲት ነጥብ ከቶ አታልፍም፥ ሁሉ እስኪፈጸም ድረስ።**

በመጀመሪያ የአዲስ ኪዳን መጽሐፍ በአጠቃላይ ማለት በሚቻል መልኩ የቅዱሳት መጽሐፍት ቃሎች ፍጻሜን ያሚገኙበት መጽሐፍ ነው የተወሰኑ ትንቢት ያዘሉ ቢኖሩም። ከላይ ባለው መነሻ ጥቅስ ውስጥ ግልጽ መሆን ያለባቸው ሀረጎች ስላሉ እነሱን አንድ በአንድ እንመልከት።

## *እነ ማን ናቸው ህግና ነብያት ሚባሉት?*

በመጀመሪያ ህግንና ነብያት ብሎ ሲገልጽ በዚያን ጊዜ እነኚ ሁለቱ አይሁድ ቅዱሳት መጻፋትን ለመግለጽ የሚጠቀሙበት አገላለጽ ነዉ ልክ እኛ ብሉይ ኪዳን ብለን እንደምንገልጸዉ ማለት ነው። ህግ ሲባል ብዙን ጊዜ ወዲያው የሚያመጣልን አስርቱ ትዕዛዛት ብቻ ናቸው። ከዚህ የተነሳ እንስታለን። ህግ ተብሎ ሲጠራ በድፍጥጡ ሳይሆ እነዚህ የሚከተሉት ነገሮች አሉት በውስጡ ፦ የቤተ - መቅደስ መስዋዕት አቀራረብ ስርአት ፤የካህናት አለባበስ ትዕዛዝ፤ የሰባቱ በአላት(የሥረየ ቀን ፤የፋሲካ ፤የቂጣ ፤የበኩራት፤የዳስ ፤የቀንደ መለከት፤የጴንጤ ቆስጤ በአላት) አከባበር ስራአት ልዩ ልዩ ህጎች በአጠቃላይ አምስቱ የሙሴ መጽሐፍትን ጭምር ነው ።

በመጽሐፍ "**ህግና ነብያት**" የሚለው ቃል ቅዱሳት መጽሐፍትን ለማመልከት እንደተጠቀሱ እንመልከታለን ፊልጶስ ናትናኤልን አግኝቶ፦ ሙሴ በሕግ ነቢያትም ስለ እርሱ የጻፉትን የዮሴፍን ልጅ የናዝሬቱን ኢየሱስን አግኝተነዋል አለው። ይህ አንደኛው ነው። ሁለተኛው ደግሞ አሁን ግን በሕግና በነቢያት የተመሰከረለት የእግዚአብሔር ጽድቅ ያለ ሕግ ተገልጦአል፥ ይህ ማለት - ሙሉ የብሉይ ኪዳን መጽሐፍን " ህግና ነብያት" በማለት ስለተገለጠው የእግዚአብሔር ጽድቅና ነብያት፤ ስለተናገሩት መሲህ በቅዱሳት መጽሐፍ እንደተነገረ ለመግለጽ ተጠቅመዋል። ጌታ እየሱስም ከሞት ከተነሳ በኋላ የእሱ ደቀመዛሙርት ለነበሩ ለኤማሁስ መንገደኞች በህግና ነብያት በመዝሙርም ስለሱ የተጻፈውን በሙሉ ተርጉሞላቸው ነበር፤ ስለዚህም ህግና ነብያት የሚለው ስለ ቅዱሳት መጽሐፍት (ብሉይ ኪዳን መጽሐፍት) ማለቱ አያጠራጥርም ማለት ነዉ።

## *"ልፈጽም" ብሎ ሲል ምን ማለቱ ነው?*

## እኔ ሕግንና ነቢያትን ለመሻር የመጣሁ አይምሰላችሁ፤ ልፈጽም እንጂ ለመሻር አልመጣሁም።

" ልፈጽም " የሚለውን ቃል እንግሊዘኛው to fulfill የሚለውን ነው የሚጠቀመው። ነገር ገን to end የሚለውን የሚጠቀምበት ቦታ አለ እሱን ስንደርስ እናያለን።

በአዲስ ኪዳን በብዙ ቦታዎች ላይ እንዲህ ተብሎ የተጻፈው ይፈጸም ዘንድ እያለ ይናገራል ፤እስቲ ምሳሌ ከህግም ከትንቢትም እንመልከት ፦ዮሐንስ 19 (አዲሱ መ.ት)

32 ስለዚህም ወታደሮቹ መጥተው ከክርስቶስ ጋር ተሰቅሎ የነበረውን
የመጀመሪያውን ሰው ጭን ሰበሩ፤ ደግሞም የሌላውን ጭን ሰበሩ።ቺ
ወደ ኢየሱስ በመጡ ጊዜ ግን ሞቶ ስላገኙት ጭኖቹን አልሰበሩም፤ ቺ
ይህም የሆነው፣ መጽሐፍ፣ ከአጥንቱ አንድም አይሰበርም ያለው
እንዲፈጸም፣ ይህ ህግ ሲፈጸም ነው። ከአጥንቱ አንድም አይሰበርም
የሚለው ይህ ህግ ሙሴ እስራኤላውያን ከግብፃ እንዲወጡ የፋሲካን
በግ አርደው ደሙን በየቤታቸው ጉበንና እና መቃን ቀብተው ቤታቸውን
እንዲያስመልጡ ግን በጉን ሲያርዱት ማድረግ ስላለባቸው ጥንቃቄ
የተናገረዉ ነው።አስተውሉ ህግ የሚባለው 10ቱ ትእዛዛት ብቻ
እንዳልሆኑ እና በ5ቱ የሙሴ መጽሐፍት ማለትም በዖሪት ዘፍጥረት
፣ዘፀዐት ፣ዘሌዋውያን ፣ዘኁልቁ፣ዘዳግም ውስጥ ያሉት በሙሉ ማለት
ነው።

ጌታ ኢየሱስ በእርሱ እንዲፈጸሙ የሚገቡ የመጽሐፍ ቃላትን እንዲት እንኳን ሳትቀር ስለእሱ የተፃፉ እንዲፈጸሙ ግድ ነው ብሎ ፤እራሱ ሐዋርያትን ሲያስተባብር ይታያል ሉቃስ 22 (አዲሱ መ.ት )[36] እርሱም እንዲህ አላቸው፤ አሁን ግን ኰረጆም፣ ከረጢትም ያለው ሰው ይያዝ፤ ሰይፍ የሌለውም ልብሱን ሸጦ ይግዛ። ፺ እላችኋለሁና፤ ከዐመፀኞች ጋር ተቈጠረ ተብሎ የተጻፈው በእኔ መፈጸም አለበት፤ ስለ እኔ የተጻፈው ፍጻሜው በርግጥ ደርሶአል። ደቀ መዛሙርቱም፣ ጌታ ሆይ፤ እነሆ፤ ሁለት ሰይፎች እዚህ አሉ አሉት። እርሱም፣ ይበቃል አላቸው።

አያችሁ!! ኢየሱስ ከአመጸኞች ጋር ተቆጠረ የሚለው እንዲፈጸም ብሎ ልብሳችሁንም እንኳን ሸጣችሁ ሰይፍ ግዙ ባማለት አዞ ነበር በኋላ ግን በጴጥሮስ እጅ ኢየሱስ የሚፈልገው ሰይፍ ስለነበረ ይበቃል!! ብሏል ይህም አመጸኞች እንዲያስብላቸው በቂ ነበርና። አይገርምም!!

እስቲ አሁን ደግሞ ከነቢያት ስለ ሚመጣው መሲህ የተነገረውን አስደናቂ ቃል እንመልከት ሉቃስ 4

[16] ወዳደገበቱም ወደ ናዝሬት መጣ፤ እንደ ልማዱም በሰንበት ቀን ወደ
ምኵራብ ገባ፥ ሊያነብም ተነሣ። ኀ-[19] የነቢዩንም የኢሳይያስን መጽሐፍ
ሰጡት፥ መጽሐፉንም በተረተረ ጊዜ፦ የጌታ መንፈስ በእኔ ላይ ነው፥
ለድሆች ወንጌልን እሰብክ ዘንድ ቀብቶኛልና፤ ለታሰሩትም መፈታትን
ለዕውሮችም ማየትን እሰብክ ዘንድ፥ የተጠቁትንም ነጻ አወጣ ዘንድ
የተወደደችውንም የጌታን ዓመት እሰብክ ዘንድ ልኮኛል ተብሎ
የተጻፈበትን ስፍራ አገኘ። ቿ መጽሐፉንም ጠቅልሎ ለአገልጋዩ ሰጠውና
ተቀመጠ፤ በምኵራብም የነበሩት ሁሉ ትኵር ብለው ይመለከቱት ነበር።
[21] እርሱም፦ ዛሬ ይህ መጽሐፍ በጆሮአችሁ ተፈጸመ ይላቸው
ጀመር።አያችሁ ይህ ትንቢት መሲሁ ሲገለጥ የሚፈፀም ስለነበረ "ዛሬ

ይህ መጽሐፍ በጆሮአችሁ **ተፈጸመ** "ብሎ ተናገረ።

ስለዚህ ህግን ልፈጽም መጣው ሲል ክርሰቶስ በመውለዱ ፣በመሞቱ፣ በመሰቀሉ ፣ በመነሳቱ ዳግመኛ በመምጣቱ የሚፈጸም (fulfill) የሚሆን ነው።

## *ታድያ እያንዳንዱ የህግ ነጥብ ተፈጽሟል ወይ?*

ሌላኛው ሀሳብ ደግሞ "ሰማይና ምድር እስኪያልፍ ድረስ፥ ከሕግ አንዲት የውጣ ወይም አንዲት ነጥብ ከቶ አታልፍም"ያለው ደግሞ ህግ ኢየሱስ ክርስቶስ በምድር በነበረበት ጊዜ ብቻ በመፈጸም የሚጠናቀቅ ሳይሆን በዳግም ምፅዓት እና እስከ አለም ፍጻሜ እንደሚቀጥል ያሳያል።

ጌታ እየሱስ ህግን ልፈጽም መጣው ያለበትን መንገድ የቤተክርስቲያን መሰረት በሆኑት ሐዋርያት እንዴት እንደተፈታ ያየነውን ከመቋጨት በፊት የእግዚአብሔር በግ ሆኖ ተገልጦ በመስቀል በመሰቀሉ የተፈጸሙትን አምስቱን በቤተ-መቅደሱ ደጃፍ ባለው ፤የክርስቶስ መስቀል ምሳሌ በሆነው የነሃስ መሰዊያ ላይ ስለሚሰውት መስዋዕትና በመስዋዕቱ ለአማኞች የተገኘውን ጥቅም እንመለከታለን። በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ ፊት ባለው የነሃስ መሰዊያ ከነዛ ከአምስቱ መስዋዕች ዉጭ ሌላ መስዋዕት አይቀርብም ምክንያቱም ኢየሱስን ብቻ የሚመለከት ስለሆነ ነው።

እግዚአብሔር በሙሴ በኩል ለእስራኤላውያን በተለይ ለአሮንና ለልጆቹም ካስተላለፋቸው የመስዋዕት ህግ ውስጥ በዋናነት አምስት አይነት መስዋዕት አለ እነሱም፦የኃጥያት መስዋዕት፤ የሚቃጠል መሰዋት ፤ የደሕንነት(የሰላም) መስዋዕት፤የበደል መስዋዕት ፤የዕህል ቁርባን መስዋዕት ናችው። የነዚህን የመስዋዕት ህጎች ሙሴ እንዴት ባለ ስርዓት መሰዋት እንዳለባቸው ያስተላለፈውን እና በክርስቶስ እየሱስ እንዴት እንደተፈጸመ እንመለከታለን። እስራኤላውያንን እግዚአብሔር በህግ መስዋዕት የሚሆን በግ ሆነ የተለያዩ ነገሮችን አምጡ ሲል እግዚአብሔር እነሱን እንዲቀበልና ላጠፋት ጥፋት በእርግጥ ምትካቸው ሊሆን የሚገባ ስለሆነ ሳይሆን ፤ይህን የሚያደርግበት ምክንያት ለእነሱ ቤዛ የሚሆን እንደሚመጣ ለማመልከት ነው። ሰለዚህ ከዚህ በመቀጠል ስለእያንዳንዱ መስዋዕት እንመልከት።

## ኢየሱስ የኃጢአት መስዋዕት

### *ሙሴ የኃጢአት መስዋዕት ህግ ስርዓትን እንዴት ዓዟል?*

ዘሌዋውያን 4

**1 እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ሲል ተናገረው፡፤ ፪ ለእስራኤል ልጆች እንዲህ ብለህ ንገራቸው፦ ማናቸውም ሰው ሳያውቅ ኃጢአት ቢሠራ፥ እግዚአብሔርም፦ አትሥሩ ካላቸው ትእዛዛት አንዲቱን ቢተላለፍ፥ ፫ የተቀባውም ካህን በሕዝቡ ላይ በደል እንዲቈጠርባቸው ኃጢአት ቢሠራ፥ ስለ ሠራው ስለ ኃጢአቱ ነውር የሌለበት ወይፈን ለእግዚአብሔር ለኃጢአት መሥዋዕት ያቀርበዋል።**

ወይፈኑንም ወደ መገናኛው ድንኳን ደጃፍ በእግዚአብሔር ፊት ያመጣዋል እጁንም በወይፈኑ ራስ ላይ ይጭነዋል፥ ወይፈኑንም በእግዚአብሔር ፊት ያርደዋል። የተቀባውም ካህን ከወይፈኑ ደም ወስዶ ወደ መገናኛው ድንኳን ያመጣዋል ካህኑም ጣቱን በደሙ ውስጥ ነክሮ በእግዚአብሔር ፊት በመቅደሱ መጋረጃ ፊት ደሙን ሰባት ጊዜ ይረጨዋል። ካህኑም በመገናኛው ድንኳን ውስጥ በእግዚአብሔር ፊት ያለው ጣፋጭ ዕጣን በሚታጠንበት መሠዊያ ቀንዶች ላይ ከደሙ ያደርጋል፤ የተረፈውንም የወይፈኑን ደም ሁሉ በመገናኛው ድንኳን ደጅ ባለው ለሚቃጠል መሥዋዕት በሚሆነው መሠዊያ በታች ያፈስሰዋል።
፰ ለኃጢአትም መሥዋዕት ከሚታረደው ወይፈን ስብን ሁሉ ይወስዳል፤ ሆድ ዕቃውን የሚሸፍነውን ስብ፥ በሆድ ዕቃውም ላይ ያለውን ስብ ሁሉ፥ ሁለቱንም ኵላሊቶች፥ በእነርሱም ላይና በጎድኑ አጠገብ ያለውን ስብ፥ በጕበቱም ላይ ያለውን መረብ ከኵላሊቶች ጋር፥ ኀ ለደኅንነት መሥዋዕት ከታረደው ወይፈን እንደ ተወሰደው ይወስዳል። ካህኑም ለሚቃጠል መሥዋዕት በሚሆነው መሠዊያ ላይ ያቃጥለዋል። ኻነ የወይፈኑን ቁርበት፥ ሥጋውንም ሁሉ፥ ራሱንም፥ እግሮቹንም፥ ሆድ ዕቃውንም፥ ኻቹ ፈርሱንም፥ ወይፈኑን ሁሉ ከሰፈሩ ወደ ውጭ አመድ ወደሚፈስስበት ወደ ንጹሕ ስፍራ ይወስደዋል፥ በእንጨትም ላይ በእሳት ያቃጥለዋል አመድ በሚፈስስበት ስፍራ ይቃጠላል።

የኃጢአት መስዋዕት ከሌላው የመስዋዕት አይነት የሚለይበት ዋናው፤ የበጉ ስጋ በሰውነቱ ካለው ከስቡ ውጭ መስዋዕት አቅራቢው እጁን በበጉ ላይ ጭኖ ኃጢአቱን ከተናዘዘ በኋላ ታርዶ ስጋው ከሰፈር ውጭ ተወስዶ ይቃጠላል። ሌላው የመስዋዕት በጉ ከታረደ በኋላ ደሙ በነሀስ መሰዊያና በመገናኛ ድንኳን ውስጥ ባለው የወርቅ መሰዊያ ከተረጨ ስጋው አይበላም፤ ይህ መስዋዕት የሚቀርበው አንድ እስራኤላዊም ሆነ ህዝቡ ወይም መሪዎች ከሙሴ ህግ አንዲቷን እንኳን ቢተላለፉ ስለኀጢአታቸው የኃጢአት መስዋዕት ያቀርባሉ ኃጢአታቸውም ይስተሰረያል።

## *የኃጢአት መስዋዕት ህግ እንዴት ተፈጸመ?*

መጽሐፍ ቅዱስ ጌታ ኢየሱስ ስለእኛ በግልጽ የኃጢአት መስዋዕት መሆኑን ሲናገር "የአለምን ኃጢአት ሁሉ የሚያስወግድ የእግዚአብሔር በግ" ይለዋል።አያችሁ! ኢየሱስ ሌሎች እሱ የሚታወቅባቸው ስሞች አሉ ለምሳሌ የአለም መድሐኒት ፤የእስራኤል ንጉስ፤የበጎች እረኛ እንዲህ አይነት ሌሎች ስሞች አሉት ምክንያቱም እየሱስ ወደ ምድር የመጣበት ምክንያት ኃጢአትን ለመክደን ሳይሆን ለማስወገድ ስለሆነም የመጣው። እንደገና ደግሞ በ(አዲሱ መ.ት) "እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንድንሆን፣ ኀጢአት የሌለበትን እርሱን እግዚአብሔር ስለ እኛ **የኀጢአት መስዋዕት** አደረገው። ይላል። እንደው አንዳንድ ሰዎች እግዚአብሔር ለምንድነው ኢየሱስን የእኛን የኀጢአት ቀንበር አሱ እንዲሸከም ለምን ያደርጋል ? ኃጢአት የሰራነው እኛ ሆነን ሳለ ይላሉ ፤ ነገር ግን እኛ ጻድቃን እንድንሆን እሱን ኃጢአት ያደረገው የአለምን ሁሉ ኃጢአት የሚያስወግድ ለኃጢአት የሚሰዋ የእግዚአብሔር በግ ስለሆነ ነው። በተጨማሪ ደግሞ በዕብራውያን መጽሐፍ ምዕራፍ 13 ይህ መስዋዕት ከሌሎች መስተዋቶች የሚለየውን

ባህርይ በመጥቀስ ጌታ ኢየሱስ ስለእኛ የኃጢአት መስዋዕት መሆኑን ያስረዳል እንዲህ በማለት ፦ "ከሊቀ ካህናት ስለ ኃጢአት ወደ ቅድስት የእንስሶችን ደም ያቀርባልና፤ ሥጋቸው ግን ከሰፈሩ ውጭ ይቃጠላል።፲፪ ስለዚህ ኢየሱስ ደግሞ በገዛ ደሙ ሕዝቡን እንዲቀድስ ከበር ውጭ መከራን ተቀበለ።"ይላል። ልክ በዚያ ዘመን ልማድ እንደነበረዉ አንድ ሰው ሰንበትን ሲሽር የተገኘም ሆነ ሌላ የሙሴን ህግ ሲተላለፍ በግልጽ የታየ ማንም ከከተማ በር ውጭ ተወስዶ በድንጋይ እንደሚወገረው ማለት ነው። አያችሁ!! ጌታ ኢየሱስ በመስቀል ተንጠልጥሎ እንዲሞት ሲደረግ ከከተማ ውጭ በዕብራይስጥ በጎልጎታ ወይም የራስ ቅል በሚባልበት ተራራ ላይ ነበር የተሰዋው። ጌታ ኢየሱስ ከሰፈር ውጭ እንዲሰቀል ምክንያት የትንቢት ቃል ስለሆነ ብቻ ሳይሆን ከተማዋ እየሩሳሌም ቅድስት የእስራኤል ንጉስ ከተማና የሰማያዊቷ እየሩሳሌም ምሳሌ ስለሆነች ፤ ነውር ማለት ኃጥያትን በግልጽ ሲያደርግ የተገኘም ሆነ በለምጽ የተመታ (የኃጥያት ምሳሌ ስለሆነ) ከእስራኤል መራቅ ስላለበት።

## *ለምን ስጋውን ብቻ?*

ሌላው ደግሞ የእግዚአብሔር ጥበብ እና ለሰው ያለውን ፍቅር ምታዩት አስደናቂ ነገር ደግሞ በሰው ስጋ ውስጥ ያለውን ኃጢአት ከሰው አውጥቶ በክርስቶስ ስጋ ውስጥ በማኖር ኃጢአትን መቅጣቱ ነው። ልክ አንዲት እናት ልጇ በካንሰር ቢያዝ በልጁ ስጋ ውስጥ ያለውን ካንሰር ትጠላው ይሆናል እንጂ ልጇን እንደማትጠላ ማለት ነው። ምክንያቱም ጳውሎስ በሮሜ መልእክቱ የምፈልገውን ያንን አላደረገም የማልፈልገው ያንን ሳደርግ እገኛለው ብሎ ይህንን እንዳደርግ የሚያደርገኝ በእኔ ማለትም በስጋዬ የሚያድር ኃጥያት ነው በማለት ኃጢያት በሰው ስጋ ወስጥ እንደሚኖርና የኃጢአት መስዋዕት ከሆነው ከበጉ ስጋውን ለምን

እንደሚለዩ በመገለጥ በመረዳት ጽፏል።ጌታ እግዚአብሔር ክብር ምስጋና ይግባውና እኛን ከነኃጢአታችን እግዚአብሔር ስላልቀጣን፤ ነገር ግን ኃጢያትን በክርስቶስ ስጋ ውስጥ በማኖር ቁጣውን በመቀበል ከፍርድና ከቅጣት በክርስቶስ ሞት አስመልጦናል።ሃሌሉያ!! “ለኃጢአት ሞተን ለጽድቅ እንድንኖር፥ እርሱ ራሱ **በሥጋው** ኃጢአታችንን በእንጨት ላይ ተሸከመ…” 1ኛ ጴጥሮስ 2፥24 አያችሁ!! ጌታ ስለሚወደን እኛ ከነኃአታችን እንዳንሞት እንዴት አይነት ጥበብ እንደተጠቀመ።አሜን!!

ከዚህ የተነሳ ደግም የተወለደ ክርስቲያን ኃጢአት ስለሌለበት ኃጢአተኛ አ..ይ..ደ..ለ..ም ነገር ግን በክርስቶስ ኢየሱስ የእግዚአብሔር ጽድቅ ሆኗል። ጽድቅ ብዙን ጊዜ በመልካም ስራ ብዛት የሚገኝ አንድ ክርስቲያ በምድር እየኖረ የሚደርሰው ግብ ይመስለዋል ነገር ግን ስ..ጦ..ታ ነው። - ሮሜ 3 ²³ ሁሉ ኃጢአትን ሠርተዋልና የእግዚአብሔርም ክብር ጎድሎአቸዋል፤ቹ በኢየሱስ ክርስቶስም በሆነው ቤዛነት በኩል እንዲያው በጸጋው ይጸድቃሉ።

## *ክርስቲያን ኅጢአትን በሰራ ቁጥር ጽድቁን ያጣል ወይ?*

ብዙን ጊዜ ዳግመኛ የተወለዱ ክርስቲያኖች ኃጥያት አድርገው ስያገኙ ጽድቃቸውን የተቀሙ ይመስላቸዋል ግን በፍጹም!! ላስረዳቹ ተመልከቱ ጽድቅ ሚለካው በእግዚአብሔር ፊት ነው የሰው ጽድቅ በእግዚአብሔር ፊት ደግሞ የመርገም ጨርቅ ነው ስለዚህ መፍትሄ ከእግዚአብሔር እራሱ ጽድቅን መፈለግ ነው ከዚህ የተነሳ ነው እግዚአብሔር ኢየሱስን የእኛ ጽድቅ አድርጎ በእርሱ ፊት ስለእኛ እንዲታይ ስጦታ አድርጎ የሰጠን። በክርስቶስ ኢየሱስ ለመሆን የበቃችሁት ከእርሱ የተነሣ ነው፤ እርሱ ከእግዚአብሔር ዘንድ ጥበባችን፣ ጽድቃችንና ቅድስናችን፣

ቤዛችንም ሆኖአል። 1ኛ ቆሮንቶስ 1፥30 (አዲሱ መ.ት) ይህ ማለት ጌታ ኢየሱስ ዘውትር በሰማይ ባለችው ድንኳን ውስጥ በአብ ፊት ስህተት ከመስራታችሁ በፊትም ሆነ በኋላ የእናንተ ጽድቅ ሆኖ በእግዚአብሔር ፊት አስታውሰው በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ ሆኖ ይታይላችዋል። ስለዚህ ነገር ሐዋርያው ዮሐንስ በድፍረት ይናገራል እንዲህ ይለናል ልጆቼ ሆይ፥ ኃጢአትን እንዳታደርጉ ይህን እጽፍላችኋለሁ። ማንም ኃጢአትን ቢያደርግ ከአብ ዘንድ ጠበቃ አለን እርሱም ጻድቅ የሆነ ኢየሱስ ክርስቶስ ነው። 1ኛ ዮሐንስ 2፥1 ዋው!! ዋው!! ደስ ሲል ምክንያቱም ህዝቡ ቢታይ ሁሌ እንከን አይጠፋበትም እግዚአብሔር ህዝቡን ሳይሆን ህዝቡን በሊቀ ካህናት በኩል ያያልና። ስለሆነም ስለራሱ ሳይሆን ስለእኛ በሰማያዊቷ ድንኳን በእግዚአብሔር ፊት ጽድቃችን ሆኖ ሊታይ የገባው ታላቁ ሊቀ ካህናችን ጌታ እየሱስ አለን። ልጆች(ክርሰቲያን) ሆነው አሁን እኳን ስህተት ቢሰሩ እንኳን በእግዚአብሔር ፊት ጻድቅ ስለመሆናችን የሚከራከር ጠበቃ ስላለን ነው።ሃሌሉያ!! ኦ......አንድ ሰው ይህ ኃጢአት ማበረታታት አይሆንም ወይ? ልትሉ ትችላላችሁ ግን አይደለም። ዮሐንስ እራሱ እንደማያበረታታ ቀድሞ ተናግሯል እንዲህ ብሎ "....ልጆቼ ሆይ፥ ኃጢአትን እንዳታደርጉ ይህን እጽፍላችኋለሁ...." "እኛ በእርሱ ሆነን የእግዚአብሔር ጽድቅ እንድንሆን፣ ኀጢአት የሌለበትን እርሱን እግዚአብሔር ስለ እኛ **የኀጢአት መስዋዕት** ስላደረገው እኛም በድፍረት ጻድቅ መሆናችንን እናውጃለን። በወንጌል የእግዚአብሔር ጽድቅ ተገልጧልና እሱም ጌታ ክርስቶስ ነው።

**"አንድ ሰው ጻድቅ ነው ማለት ስለ እርሱ በእግዚአብሔር ፊት የሚታይለት ጻድቅ ሰው አለው ማለት ነው።"**

## ኢየሱስ የሚቃጠል መስዋዕት

### *ሙሴ የሚቃጠል መሰዋዕት ህግ ስርዓትን እንዴት አሟል?*

# ዘሌዋውያን 1

¹ እግዚአብሔርም ከመገናኛው ድንኳን ውስጥ
ሙሴን ጠርቶ እንዲህ ሲል ተናገረው፦ ቹለእስራኤል
ልጆች እንዲህ ብለህ ንገራችው፦ ከእናንተ
ማናቸውም ሰው ለእግዚአብሔር መባ ሲያቀርብ
መባችሁን ከእንስሳ ወገን ከላሞች ወይም ከበጎች
ታቀርባላችሁ። ቺ መባውም የሚቃጠል መሥዋዕት
ከላሞች መንጋ ቢሆን፥ ነውር የሌለበትን ተባቱን
ያቀርባል፤ በእግዚአብሔር ፊት እንዲሠምር
በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ ፊት ያቀርበዋል።
እጁንም በሚቃጠለው መሥዋዕት ራስ ላይ
ይጭናል፤ ያስተሰርይለትም ዘንድ የሠመረ
ይሆንለታል። በሬውንም በእግዚአብሔር ፊት
ያርደዋል፤ የአሮንም ልጆች ካህናቱ ደሙን ያቀርባሉ፤
ደሙንም በመገናኛው ድንኳን ደጃፍ ፊት ባለው
በመሠዊያው ላይ በዙሪያው ይረጩታል።
የሚቃጠለውንም መሥዋዕት ይገፍፈዋል፥
በየብልቱም ይቈርጠዋል። የካህኑም የአሮን ልጆች
በመሠዊያው ላይ እሳት ያነድዳሉ፥ በእሳቱም ላይ
እንጨት ይደረድራሉ፤ የአሮንም ልጆች ካህናቱ
የተቈረጡትን ብልቶች ራሱንም ስቡንም
በመሠዊያው ላይ በእሳቱ ላይ ባለው በእንጨቱ ላይ
ይረበርቡታል፤ የሆድ ዕቃውንና እግሮቹን ግን በውኃ
ያጥባል፤ ካህኑም ሁሉን የሚቃጠል መሥዋዕት
የእሳት ቍርባን አድርጎ በእግዚአብሔር ዘንድ ጣፋጭ
ሽታ እንዲሆን በመሠዊያው ላይ ያቃጥለዋል።

የዚህ መስዋዕት አቀራረብ ስርአት ከሌላው የሚለየው የመስዋዕቱ ምኑም ሳይቀር የሆድ ዕቃው እንኳን ሳይቀር ታጥቦ ፤ ስቡም የሚበላውም ስጋ ተቆራርጦ ሁለንተናው ይቃጠላል፤እግዚአብሔርም በመስዋዕቱ ሽታ **ደስ** ይሰኛል።

## *የሚቃጠል መስዋዕት ህግ እንዴት ተፈጸመ?*

ከአዳም ውድቀት በኋላ ከሰው ልጆች አንድም እግዚአብሔርን ሊያስደስተው የሚችል በምድር አልተገኘም ነበር። እግዚአብሔር በብሉይ ኪዳን እሱን ደስ ስለሚያሰኘው በሚስጢር ለቅዱሳን አባቶች ይናገር ነበር ፤ እርሱም ማን እንደሆነ ተግተው ይፈለጉም ይመረምሩም ነበሩ፦ (መዝሙር 27፥4) “እግዚአብሔርን አንዲት ነገር ለመንሁት እርስዋንም እሻለሁ፤ በሕይወቴ ዘመን ሁሉ በእግዚአብሔር ቤት እኖር ዘንድ፥ **እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘውንም አይ ዘንድ**፥ መቅደሱንም እመለከት ዘንድ። ብሎ ዳዊት በመዝሙሩ በጸሎት መንፈስ ሆኖ እግዚአብሔርን አጥብቆ አንዲት ነገር ይለምናል እሱም "እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘውንም አይ ዘንድ"እያለ፤ አያችሁ!! እሱ እየጠየቀ ያለው ነገር፦ ደስ የሚያሰኘውን **አደርግ** ዘንድ ሳይሆን **አይ** ዘንድ ነው ያለው።ስለዚህ አደርግ ዘንድ ቢል ምናልባት እግዚአብሔር ይሄን አድርግ ያንንም አድርግ ይለው ነበር ግን አይ ዘንድ ስላለ መመልከት የሚፈልገው የሆነ ሰው ወይም ስብዕና( person) ነው ማለት ነዉ።እስቲ ይህ ደስ የሚያሰኘው ማን እንደሆነ እንመልከት ፦ ምሳሌ 8 [28] ደመናትን በላይ ባዘጋጀ ጊዜ፥ የቀላይን ምንጮች ባጸና ጊዜ፥ቹ ለባሕርም ዳርቻን በወሰነ ጊዜ ውኃ ከትእዛዙ እንዳያልፍ፥ የምድርን መሠረት በመሠረተ ጊዜ፥ቺ የዚያን ጊዜ እኔ በእርሱ ዘንድ ዋና ሠራተኛ

ነበርሁ፤ ዕለት ዕለት **ደስ** አሰኘው ነበርሁ፥ በፊቱም ሁልጊዜ **ደስ** ይለኝ ነበርሁ፥ በዚህ መጽሐፍ ምዕራፍ ውስጥ የሚያወራው ስለጥበብ ነው ይህ ጥበብ ደግሞ ጳውሎስ በአንደኛ ቆሮንቶስ ለተጠሩት ግን፥ አይሁድ ቢሆኑ የግሪክ ሰዎችም ቢሆኑ፥ የእግዚአብሔር ኃይልና የእግዚአብሔር ጥበብ የሆነው ክርስቶስ ነው።"ብሎታል ታድያ እግዚአብሔር ሰማያትን ሲሰራ ከእርሱ ጋር ከሆነ እለት እለት እግዚአብሔርን ደስ የሚያሰኘው በእርሱ ከሆነ ፤ ጌታም በእግዚአብሔር ደስ የሚሰኝ ከሆነ ያ ዳዊት ደስ የሚያሰኝህን ማየት እፈልጋለሁ ብሎ የተናገረው ክርስቶስ ነው ማለት ነዉ።በሚገርም መንገድ ደግሞ በአዲስ ኪዳን እግዚአብሔር ሰማያትን ከፍቶ ሁለት ጊዜ "በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ እሱ ነው እሱን ስሙት" ብሏል። ታድያ እግዚአብሔር በእየሱስ መደሰቱ ለኛ ምን ይጠቅማል? ትሉ ይሆናል እዚህጋ ነው ዋናው። ጌታ እየሱስ እራሱን የሚቃጠል መስዋእት አድርጎ በእግዚአብሔር ፊት ማቅረቡን በኤፌሶን 5 ላይ ይናገራል ፤ከዚህም የተነሳ በእግዚአብሔር ፊት ተወዳጆች አድርጎናል።

1 እንግዲህ እንደ ተወደዱ ልጆች እግዚአብሔርን የምትከተሉ ሁኑ፥ቹ ክርስቶስም ደግሞ እንደ ወደዳችሁ ለእግዚአብሔርም የመዓዛ ሽታ የሚሆንን መባንና መሥዋዕትን አድርጎ ስለ እናንተ ራሱን አሳልፎ እንደ ሰጠ በፍቅር ተመላለሱ።

እግዚአብሔር እኛን የወደደበት መክንያት ኢየሱስ ራሱን መልካም መዓዛ ያለው ወይንም እግዚአብሔርን የሚያስደስት መባና መስዋዕት አድርጎ ስለእኛ ራሱን ስላቀረበ ነው። በድጋሚ እግዚአብሔር አብ ያለውን ላስተውሳቹ "በእርሱ ደስ የሚለኝ የምወደው ልጄ" ነው ያለው ስለዚህ ኢየሱስን እግዚአብሔር አብ የሚወደው ስለሚያስደስተው ነው ማለት ነው። ስለዚህ ጌታ አሁን እራሱን ስለእኛ እንጂ ስለራሱ መስዋዕት

ስላልሆነ ኢየሱስ በእግዚአብሔር ፊት እለት እለት እንደሚያስደስተው እግዚአብሔር በክርስቶስ ኢየሱስ እለት እለት በእኔ ይደሰታል፤ ስለዚህም **ይወደኛል** ።ጌታ ኢየሱስ በዮሐንስ ወንጌል 17 ላይ እንደ ሊቀ ካህናት ሆኖ በሚፀልይበት ቦታ የደቀ መዛሙርቱና በእርሱ ስለሚያምኑት ሲፀልይ እንዲህ ብሎ ብሎ ነበር እኛም አንድ እንደ ሆንን አንድ ይሆኑ ዘንድ፤ እኔም በእነርሱ አንተም በእኔ ስትሆን፥ በአንድ ፍጹማን እንዲሆኑ፥ የሰጠኸኝን ክብር እኔ ሰጥቻቸዋለሁ፤ እንዲሁም ዓለም አንተ እንደ ላክኸኝ በወደድኸኝም መጠን እነርሱን እንደ ወደድሃቸው ያውቃል። ዮሐንስ 17፥22-23

ጌታ በዚህ ቦታ የሚናገረው እግዚአብሔር እሱን በሚወድበት ልክ ደቀ-መዛሙርቱንና በእርሱ የሚያምኑትን እንደሚወድና እንዳስታወቃቸው ሲናገር ነው ሚሰማው ፤ ልክ የእግዚአብሔር መንፈስ ለእግዚአብሔር ያለውን ጥልቅ ነገር እንኳን ሳይቀር ይመረምራል እንደሚል ፤አብን ያየ ፣ከእቅፉ የወጣው ፣ለአብ ያለውን ሁሉ የሚያውቀው ልጁ ሲናገር ማለት ነው። ምክንያቱም እርሱ ስለእኛ የሚቃጠል መስዋዕ ስለሆነልን ነውና።ለዚህ ነው ሐዋርያት በመልእክታቸው "ተወዳጆች ሆይ" ይሉናል በነሱ ሳይሆ በማ እንደተወደድን እያመለከቱ። "እግዚአብሔር እኔ አልለወጥ" ብሏልና በማይለወጥ ፍቅር ይወደናል።የሰው ፍቅር ለእርሱ ባለው ሳይሆ እርሱ ለሰው ስላለው ፍቅር አይለወጥም አይቀየርም!!! ይህ ልብን በእምነት የሚሞላ እውነት ነውና በእምነት እንዲህ እናውጃለን" [5]... እርሱ ራሱ፦ አልለቅህም ከቶም አልተውህም ብሎአልና፤ ስለዚህ በድፍረት፦ ጌታ ይረዳኛልና አልፈራም፤ ሰው ምን ያደርገኛል? እንላለን።" ዕብራውያን 13 ሃሌሉያ!!

## *ክርስቲያን ስህተት ቢሰራ የእግዚአብሔር ፍቅር ይለወጥበታል ወይ?*

ሌላው ደግሞ ክርስትያኖች በየእለቱ የሚሰሩት ስህተት ሲቀንስ ደስ የሚለው ሲበዛ ደግሞ እግዚአብሔር የሚቆጣ ይመስላቸዋል ግን አይደለም!! ምክንያቱም እግዚአብሔር እኔን እንዲወድና እንዲደሰት ምክንያቱ ኢየሱስና ኢየሱስ ብቻ ነው። ስለዚህ ስህተት ብሰራ እንኳን ደስታው በእኔ ላይ ፍጹም ነው ፤ ለኔ ያለው ፍቅር በእኔ በጎ ወይም ክፉ ድርጊት አይቀንስም አይጨምርም፤ የደስታው ምክንያት ስለእኔ በመስቀል የሞተው ልጁ እለት እለት ስለየሚያስደስተው ነው።ስለዚህ ትኩረታችሁን ከራሳቹ ላይ አንስታችሁ ክርስቶስ አድርጉ።

ለዚይህ ነው እግዚአብሔር ሁሌም በሰውዬው ምትክ መስዋዕቱን የሚቀበለው ሰው ሁሌ በእግዚአብሔር ፊት ደካማና እንከን ያለበት ስሆነ በእኛ ምትክ ክርስቶስን ይቀበላል።የሰው ጽድቅ (መልካም ስራ) እንኳን በእግዚአብሔር ፊት የመርገም ጨርቅ ነውና።

**"አንድ ሰው ለራሱ ጠበቃም ሆነ ምትክ ሲያቀርብ እርሱ ብቁ አለመሆኑን ያመለክታል።"**

## ኢየሱስ የደኅንነት/የሠላም መስዋዕት

### *ሙሴ የሠላም መስዋዕት ህግ ስርዓትን እንዴት አዟል?*

ዘሌዋውያን 3

**1 ቍርባኑም የደኅንነት መሥዋዕት ቢሆን፥ ከላሞች መንጋ ተባት ወይም እንስት ቢያቀርብ፥ ነውር**

**የሌለበትን በእግዚአብሔር ፊት ያቅርብ። ፰ እጁንም ለቍርባን በቀረበው ራስ ላይ ይጭናል፥ በመገናኛውም ድንኳን ደጃፍ አጠገብ ያርደዋል፤ የአሮንም ልጆች ካህናቱ ደሙን በመሠዊያው ላይ በዙሪያው ይረጩታል። ፱ ከደኅንነቱም መሥዋዕት ለእግዚአብሔር የእሳት ቍርባን አድርጎ ያቀርባል፤ የሆድ ዕቃውን የሚሸፍነውን ስብ፥ በሆድ ዕቃውም ላይ ያለውን ስብ ሁሉ፥ ሁለቱንም ኵላሊቶች፥ በእነርሱም ላይና በጎድኑ አጠገብ ያለውን ስብ፥ በጉበቱም ላይ ያለውን መረብ ከኵላሊቶች ጋር ይወስዳል። የአሮንም ልጆች ከሚቃጠል መሥዋዕት ጋር በመሠዊያው ላይ በእሳቱ ላይ ባለው በእንጨቱ ላይ ያቃጥሉታል፤ የእሳት ቍርባን ለእግዚአብሔር ጣፋጭ ሽታ ነው።**

የዚህ መስዋዕት ስም በትውፊት የሰላም መስዋዕት በመባል ይታወቃል እንዲሁም በአብዛኛው በእንግሊዝኛ በተተረጎሙ የመጽሐፍ መቅደሱ ቅጂዎች (peace offering) የሚለዉን ይጠቀማሉ እኔም የሠላም መስዋዕት የሚለውን እጠቀማለሁ። በመደበኛው ትርጉም የደህንነት መስዋዕት በሚል ይታውቃል ነገር ግን በአዲሱ መ.ት የኅብረት መስዋዕት ይባላል። ብዙውን ጊዜ ይህ የመስዋዕት አይነትና የሚቃጠል መሰዋዕት በግለሰብ ደረጃም ይደረጋል በተለይ በህብረት እስራኤላውያን ከምርኮ ሲመለሱ፤ ህዝቡ በሙሉ ሲበድ፤ በነዚህ መስዋዕት ከእግዚአብሔር ጋር ያላቸውን ግንኙነት ያድሳሉ።መስዋዕት ከሚሆነው እንስሳ ስብ ካለበት ከሰውነቱ አካል ወስደው ያቃጥሉታል ስጋውን ግን ካህናት ይበሉታል በዚህ ከሌሎች መስዋዕት ይለያል።

## *የሠላም መስዋዕት ህግ እንዴት ተፈጸመ?*

የሰው ልጅ በእግዚአብሔር ላይ ማመጽ ከጀመረበት ጊዜ ጀምሮ በሰው እና በእግዚአብሔር መካከል ጥል ነበር። የአዳም ልጆች ምን ያህል ከኃጢአት የተነሳ ከእግዚአብሔር ጋር ጠላቶች እንደሆኑ የሚያሳዩን ብዙ ነገሮች አሉ።እንደው በምን? ብትሉ እግዚአብሔር የቀድሞውን በኖህና በሎጥ ዘመን ያለውን ትውልድ ከኃጢአት የተነሳ ያለርህራሄ በእሳት ዲንና በውሃ አጥፍቷል ከዚያ በኋላ እስራኤልን በአብርሃም በኩል ከመረጠው በኋላ ኪዳንን በመድረግ በሌዊ ነገድ በኩል የክህነትን አገልግሎት በመጠቀም መስዋዕት በማቅረብ ሠላምን ሲፈጥር ፤ አህዛብ የተባልነውን ደግሞ በተቃራኒ ያለ ተስፋና ለኪዳኑ ባእዳን በመሆን በጠላትነት ቀጥለን ነበር።እስራኤል የእግዚአብሔር ቅዱስ ህዘብ ከሆነ በኋላ እነሱ ከግብፅ ወጥተው በመንገድ ላይ ሳሉ እግዚአብሔር ለሙሴ እንዲህ ብሎ ነበር "ወደ ከነአን ስትገባ አንድም ሳታስቀር አጥፋቸው የሠላምም ውል አትዋዋል " ነበር ያለው ፤እያሱ ዮርዳኖስን ወንዝ ተሻግሮ ከነአናውያን ላይ ጦር ሲያዘምት 31 ነገስታትና ህዝቦቹን ከህጻን እስከ አዋቂ አንዲት ነብስ እንኳን ሳትቀር በሰይፍ ስለት ነበር ያጠፏቸው። አያችሁ!! ይህ ምን ያህል አህዛብ ከእግዚአብሔር ጋር ጠላቶች እንደነበርን ያሳያል።

የሠላም ወይም የደህንነት መስዋዕት አብዛኛውን ጊዜ ህዝቡ በሙሉ ከእግዚአብሔር ጋር ያለውን ህብረት ለማደስ ፤ግንኙነቱ የሠላምና ደህንነቱ የተረጋገጠ ለማድረግ ፤ ህዝቡ በድሎም ከሆነ ከእግዚአብሔር ጋር ሠላም ለመሆን ይህን መስዋዕት ያቀርባሉ። በአዲስ ኪዳን ደግሞ አሁን ጌታ እየሱስ እኛ ከእግዚአብሔር ጋር ታርቀን ሠላም እንድንሆን መስዋዕት ሆኖልናል። መጽሐፍም ስለዚህ እንድህ ይላል ፦ቆላስይስ 1 (አዲሱ መ.ት)[20] በመስቀሉ ላይ በፈሰሰው ደሙ **ሰላምን** በማድረግ

በምድርም ሆነ በሰማይ ያለውን ነገር ሁሉ በእርሱ በኩል ከራሱ ጋር አስታረቀ።ቹ1 ከክፉ ባሕርያችሁ የተነሣ ቀድሞ ከእግዚአብሔር የተለያችሁ በአሳባችሁም ጠላቶች ነበራችሁ።ቹቹአሁን ግን ነውርና ነቀፋ የሌለባችሁ ቅዱሳን አድርጎ በእርሱ ፊት ሊያቀርባችሁ፣ በክርስቶስ ሥጋ በሞቱ በኩል አስታረቃችሁ።

ጌታ ኢየሱስ በመስቀል ራሱን መስዋዕት በማድረግ በሰማይ ያለውን እግዚአብሔርን በምድር ያለነውን የሰውን ልጆችን በተግባራችን ብቻ ሳይሆን በሀሳባችን ጭምር ጠላቶች የነበርነውን በመስቀል በፈሰሰው ደም አስታርቆ ሠላምን አድርጓል። ክርስቶስም በመስቀሉ ሰላምን ስላወጀ ቀድሞ ከኃጢአት የተነሳ የተለየነውን እግዚአብሔርን በልጁ ደም አስታርቆን፤ በዳንነው በልጆቹ በኩል ደግሞ ታረቁኝ! ታረቁኝ! ይላል ምክንያቱም በልጁ በክርስቶስ ኢየሱስ ሥራ ስለረካ። እንዲሁም በሌላ ስፍራ ደግሞ ኤፌሶን 2 (አዲሱ መ.ት)[11] ስለዚህ እናንተ ቀድሞ በትውልድ አሕዛብ የሆናችሁ፣ በአካል ላይ በሰው እጅ ከተደረገው የተነሣ፣ ራሳቸውን ተገርዘናል በሚሉት፣ ያልተገረዙ የተባላችሁ ያን አስታውሱ፤ኀቹ በዚያን ዘመን ከክርስቶስ ተለይታችሁ፣ ከእስራኤል ወገንነት ርቃችሁ፣ ለኪዳኑም ተስፋ ባዕዳን ሆናችሁ፣ በዓለም ላይ ያለ ተስፋና ያለ እግዚአብሔር እንደ ነበራችሁ አስታውሱ።ኀቺ አሁን ግን እናንተ ቀድሞ ርቃችሁ የነበራችሁ፣ በክርስቶስ ኢየሱስ ሆናችሁ በክርስቶስ ደም አማካይነት ቀርባችኋል።ኀ ሁለቱን አንድ ያደረገ፣ የሚለያየውንም የጥል ግድግዳ ያፈረሰ **ሰላማችን** እርሱ ራሱ ነውና፤ኀ ሕግንም፣ ከትእዛዛቱና ከሥርዐቱ ጋር በሥጋው ሻረ። ዐላማውም ከሁለቱ አንድን አዲስ ሰው በራሱ ፈጥሮ **ሰላምን** ለማድረግ ነው።ኀ ጥልን በገደለበት በመስቀሉም ሁለቱን በዚህ በአንድ አካል ከእግዚአብሔር ጋር አስታረቀ።

ኢየሱስ ለእኛ የኃጢአትና የሚቃጠል መስዋዕት እንደሆነ ሁሉ የሠላም መስዋዕት ሆኖ ከአብ ስላስታረቀን " **ኢየሱስ ሠላማችን ነው**" እንላለን። ጌታ ኢየሱስ ሲሞትና ከእግዚአብሔር ጋር ሲያስታርቀን፤ በህግ ያለ አህዛብን ሲቃወምና ሲጻረር የነበረውን ህግና ስርዓቱንም ጭምር አስወግዶ ነው። እግዚአብሔርም በህጋቸው ከአህዛብ ጋር እንዳይተባበሩ ፣ልጆቻቸውን ለአህዛብ ወንዶችንና ሴቶች ልጆች እንዳይሰጡም እንዳይቀበለው ታዘዋል ፣እኛም አህዛብ በእነሱ ዘንድ እንደ ውሻ ነበር የምንታየው ፤ነገር ግን ጌታ ይህን ጥል በመስቀል ገድሎ እኛንም እስራኤልንም በአንድ መንፈስ ወደ አብ እንድንገባ አደረገን። ለዚህ ነው መጽሐፍ " **እሱ ሠላማችን ነው!** "ይላልና። ሃሌሉያ!!

## ኢየሱስ የበደል መስዋዕት

### *ሙሴ የበደል መስዋዕት ህግ ስርዓትን እንዴት አዟል?*

ዘሌዋውያን 5

**14 እግዚአብሔርም ሙሴን እንዲህ ሲል ተናገረው፦ነ ማናቸውም ሰው ቢበድል፥ ሳያውቅም ለእግዚአብሔር በተቀደሰው በማናቸውም ነገር ኃጢአትን ቢሠራ፥ ለበደል መሥዋዕት ለእግዚአብሔር ከመንጋ ነውር የሌለበትን አውራ በግ ያቀርባል፤ እንደ ግምጋሜህ መጠን በብር ሰቅል እንደ መቅደሱ ሰቅል ሚዛን ለበደል መሥዋዕት ያቀርበዋል።ነ በተቀደሰ ነገር ላይ ስለ ሠራው ኃጢአት ዕዳ ይከፍላል፥ አምስተኛውንም እጅ ይጨምርበታል፥ ለካህኑም ይሰጠዋል። ካህኑም በበደል መሥዋዕት አውራ በግ ያስተሰርይለታል፥**

**እርሱም ይቅር ይባላል።ኀ ማናቸውም ሰው ኃጢአት ቢሠራ፥ እግዚአብሔርም፦ አትሥሩ ካላቸው ትእዛዛት አንዲቱን ቢተላለፍ፥ ባያውቅም፥ ያ ሰው በደለኛ ነው፥ ኃጢአቱንም ይሸከማል።ኀ ነውር የሌለበትን አውራ በግ ከመንጋው ለበደል መሥዋዕት እንደ ግምጋሜህ መጠን ወደ ካህኑ ያመጣዋል ካህኑም ሳያውቅ ስለ ሳተው ስሕተት ያስተሰርይለታል፥ እርሱም ይቅር ይባላል።ኀ እርሱም የበደል መሥዋዕት ነው፤ በእውነት በእግዚአብሔር ፊት በደለኛ ነው።.....**

የበደል መስዋዕት የሚቀርብበት ምክንያት ተብሎ የተጠቀሱ ከላይ እንደምናየው ናቸው ፤ በሌላ ስፍራ ደግሞ ከተላላፊ የቆዳ በሽታ ለመንፃት የሚደረጉ መስዋዕት ፤አንድ ወንድ በሌላ ሴት ላይ ጥቃት ፈጽሞ ሲገኝ በነዚህ እና በተለያዩ ምክንያቶች ይህ አይነት መስዋዕት ይቀርባል። አቀራረቡ እንደ ሠላም መስዋዕት ሆኖ ስቡ ሲቃጠል ስጋው ደግሞ ካህናት በልተው የታረደውን በግ ደም በመሰዊያ ላይ ይረጫሉ።

## *የበደል መስዋዕት ህግ እንዴት ተፈጸመ?*

ኢሳይያስ 53

5 እርሱ ግን ስለ መተላለፋችን ቈሰለ፥ ስለ **በደላችንም** ደቀቀ፤ የደኅንነታችንም ተግሣጽ በእርሱ ላይ ነበረ፥ በእርሱም ቍስል እኛ ተፈወስን። እኛ ሁላችን እንደ በጎች ተቅበዝብዘን ጠፋን፤ ከእኛ እያንዳንዱ ወደ ገዛ መንገዱ አዘነበለ፤ እግዚአብሔርም የሁላችንን **በደል** በእርሱ ላይ አኖረ።

ስለዚህ ጌታ ኢየሱስ በመሰዊያው ላይ ስለእኛ ሲሰዋ እግዚአብሔር የእኛን በደል በእሱ ላይ አኑሮ እኛን ደግሞ ነጻ ሲያወጣን ሲታረቀንም በደላችንን አይቆጥርብንም ነበር።በደላችንንም ከከተማ ውጭ ምድረበዳ ተወስዳ መታሰቢያዋ እስኪጠፉ ድረስ እንደምትባረረው የፍየል መስዋዕት በደላችንንና ኃጥአታችንን ረስቷል ፤ከእንግዲህም ለዘላለም አያስታውስም።

## ኢየሱስ የእህል ቁርባን

### *ሙሴ የእህል ቁርባንን መስዋዕት ህግ እንዴት አዟል?*

ዘሌዋውያን 2

**1 ማናቸውም ሰው የእህል ቍርባን ለእግዚአብሔር ሲያቀርብ ቍርባኑ ከመልካም ዱቄት ይሁን፤ ዘይትም ያፈስስበታል፥ ዕጣንም ይጨምርበታል፤፪ ወደ አሮንም ልጆች ወደ ካህናቱ ያመጣዋል፤ ከመልካም ዱቄቱና ከዘይቱም አንድ እፍኝ ሙሉና ዕጣኑን ሁሉ ወስዶ ካህኑ የእሳት ቍርባን ለእግዚአብሔር ጣፋጭ ሽታ እንዲሆን ለመታሰቢያ በመሠዊያው ላይ ያቃጥለዋል።፫ከእህሉም ቍርባን የተረፈው ለአሮንና ለልጆቹ ይሆናል፤ ይህም ለእግዚአብሔር የሚሆን የእሳት ቍርባን ቅዱሰ ቅዱሳን ነው።**

የእህል ቁርባን መስዋእት ከኃጢአት ጋር የተገናኘ ነገር የለውም በተጨማሪ ደግሞ እህሉ በጨው በቅባትና በእጣን ይቀመማል ከዛ ለመታሰቢያነት ይቆርሱና የተወሰነውን የአሮን ልጆች ቅድስት በሆነችው በመገናኛው ድንኳን ውስጥ ይበላሉ፤ የቀረው ይቃጠላል ነገር ግን እርሾ የኃጢአት ምሳሌ ሰለሆነ አይቀላቀሉትም።

## *የእህል ቁርባን መስዋዕት ህግ እንዴት ተፈጸመ ?*

የእህል ቁርባን መስዋእት ብዙን ጊዜ ከሚቃጠል መስዋዕት ጋር ነው የሚፈጸመው ምክንያቱም ከዚህ በፊት ስለሚቃጠለው መስዋዕት ስናወራ እንዳየነው ኢየሱስ በመስቀል ላይ በሰራው ሥራ እኛን በእግዚአብሔር እንድንወደድ እንዳደረገን አይተናል ይህም የሆነው የራሱን ሰውነት አሳልፎ በመስጠት ነው። ጌታ ሊሰቀል በሚወሰድበት ምሽት የተናገረውን ጳውሎስ አስታውሶ ጌታ ኢየሱስ አልፎ በተሰጠበት በዚያች ሌሊት እንጀራን አንሥቶ አመሰገነ፥ ቆርሶም፦ እንካችሁ ብሉ፤ ይህ ስለ እናንተ የሚሆን ሥጋዬ ነው፤ ይህን **ለመታሰቢያዬ** አድርጉት አለ። — 1ኛ ቆሮንቶስ 11፥24 ጌታ ስጋውን ስለዓለም ሁሉ ኃጢአት መስጠቱን ያሳያል እግዚአብሔርም ስለ መስዋቱ እጅግ ደስ ይለዋል ምክንያቱም እሱ ከኃጢአት በቀር በሁሉ የተፈተነ አንዳችም ኃጢአት የሌለበት ፤ያላደረገ ነውና። ዮሐንስ ... በእርሱም ኃጢአት የለም..."(በሰውነቱ) ጴጥሮስ ....እርሱም ኃጢአት አላደረገም..." (በድርጊት) ብለው ፍጹምና እንከን አልባ መሆኑን መስክረዋ ከዚህ የተነሳ እርሾ በቁርባኑ አለመጨመሩ ጥላ ሆኗል።ሌላው ደግሞ የአሮን ልጆች ለመታሰቢያነት ሊቃጠል ካለው ቁርባን መብላታቸው ነው ይህም ክርሰቲያኖች በጌታ እራት ስርአት ውስጥ እንጀራውን ስንወስድ የጌታን መሰቀል እናስታውሳለን ለዛ ነው"ለመታሰቢያነት ያቃጥለዋል" ይላልና፤ ሰለጌታም ለመመስከር እንነሳሳለን ፤ቁርባኑ እጅግ ቅዱስ ሰለሆነ

በቅዱሳን ጉባኤ ጌታ ባለበት ነው ፤በግዴለሽነት መውሰድም የለብንም።በመጨረሻም ቁርባኑ በቅባት የመቀመሙ ሚስጥር ጌታ በመንፈስ ቅዱስ መቀባቱ ነው።

ኢየሱስ የኃጢአት የሚቃጠል የሠላምና የበደል መስዋዕት በግ ሆኖ በአብ ፊት ነውር የሌለው ሆኖረ በዘላለም መንፈስ ራሱን ለእግዚአብሔር አቅርቧል። ይህ ማለት የኢየሱስ መስዋዕትነት በአብ ፊት ስለሚታይ እኛንም በዛ መስዋዕት በኩል ነው የሚያየው።ለዚህ ነው ሐዋሪው ዮሐንስ በራዕይ መጽሐፍ እሱ ወደ ሠመያዊቷና እዉነተኛዋ ድንኳን ሲገባ በእንስሶችና በሽማግሌዎች መካከል ጌታን እንደ **ታረደ በግ** ቆሞ አየሁት ያለው። ማለት መስዋዕት ሆኖ ማለት ነዉ።

ስለዚህ ጌታ ኢየሱስን በኃጢአት መስዋዕት ሲያጸድቀን በሚቃጠለው መስዋዕት ተወዳጆች ሲያደርገን፤ በደሕንነቱ መስዋዕት ሠላም ሲፈጠር በበደሉ መስዋዕት ኃጢአታችንን ይቅር ብሎ ቁርባኑ ደግሞ ስጋውን እንድንካፈል አደረገን።

## "በነሃሱ መሰዊያ የሚቀርቡት የአምስቱም መስዋዕት ህግ ፍጻሜው ጌታችን መድሀኒታችን ኢየሱስ ክርስቶስ ነው።"

በመጨረሻ በልዩ ልዩ በአላቶች ላይ የሚቀርቡ የእህልና የተመለከትናቸው ሚመስሉ መስዋዕቶች አሉ ከእነዚህ ጋር አንድ ላይ የሚቀርብ የመጠጥ ቁርባን መስዋዕት አለ። ይህ ቁርባን በተቀደሰ ስፍራ በማፍሰስ/በመድፋት ነው የሚፈጸመው። ይህ መጠጥ የሚሰራው ከወይን ነዉ ወይን ደግሞ የሚያመለክተው ደምን ነው።ሐዋርያው

ጳውሎስ በአገልግሎቱ መጨረሻ ላይ ለመንፈሳዊው ልጁ ጢሞቴዎስ እንዲህ ብሎ ነበር 2ኛ ጢሞቴዎስ 4 (አዲሱ መ.ት) [6] እኔ እንደ መጠጥ ቍርባን መሥዋዕት ለመፍሰስ ተቃርቤአለሁ፤ ተለይቼ የምሄድበት ጊዜ ደርሶአል። መልካሙን ገድል ተጋድያለሁ፤ ሩጫውን ጨርሻለሁ፤ ሃይማኖትንም ጠብቄአለሁ።

ህይወቴን እንደ **መጠጥ ቁርባን** መስዋዕት ሊፈስ ተቃርቧል በማለት ስለወንጌ እንደሚሰዋ አስቀድሞ ተናግሯል በነዚህም በመገናኛው ድንኳን ውስጥ በደቡብ በኩል ባለው የህብስት ማስቀመጫ በሆነው ጠረጴዛ ላይ የሚቀመጠውን ከወይን የተሰራውን የመጠጥ ቁርባን ፍቺ ተናግሯል። በተመሳሳይ በዮሐንስ ራእይ 6 (አዲሱ መ.ት)

" [9] አምስተኛውን ማኅተም በፈታ ጊዜ፣ ስለ እግዚአብሔር ቃልና ስለ ጠበቁትም ምስክርነት የታረዱትን ሰዎች ነፍሶች ከመሠዊያው በታች አየሁ።

[10] እነርሱም በታላቅ ድምፅ፣ ሁሉን የምትገዛ ቅዱስና እውነተኛ ጌታ ሆይ፤ እስከ መቼ አትፈርድም? እስከ መቼስ ደማችንን በምድር በሚኖሩት ላይ አትበቀልም?” አሉ። "ይላል።

ስለዚህ ይህ የመጠጥ ቁርባን ጥላ የሆነው ስለ ቅዱሳን መስዋዕትነት ነው።

እነዚህ የተመለከትናቸው ኢየሱስ በሞቱና በትሳዔው የተፈጸሙ (fulfilled) የተደረጉ ድንቅ ሚስጥራት ናቸው። ግን ደግሞ ፍጸሜን ያላገኙ ህግጋት አሉ ለምሳሌ የቀንደ መለከት በአል ገና ፍጻሜውን አላገኘም ፤ የቀንደ መለከት በአል ፍፃሜው እንደ መፅሐፍ ቅዱስ፤ ኢየሱስ ዳግመኛ በሚመጣበት ስለሚሆነው ሲናገር፦ማቴዎስ 24

30 የሰማያትም ኃይላት ይናወጣሉ። በዚያን ጊዜም የሰው ልጅ ምልክት
በሰማይ ይታያል፥ በዚያን ጊዜም የምድር ወገኖች ሁሉ ዋይ ዋይ ይላሉ፥
የሰው ልጅንም በኃይልና በብዙ ክብር በሰማይ ደመና ሲመጣ ያዩታል፤
31 መላእክቱንም ከታላቅ መለከት ድምፅ ጋር ይልካቸዋል፥ ከሰማያትም
ዳርቻ እስከ ዳርቻው ከአራቱ ነፋሳት ለእርሱ የተመረጡትን
ይሰበስባሉ።በዚህ የተነሳ የዚህ ህግ (በአል) ፍፃሜው ዳግም ምፅዐት
ነው ማለት ነው።በህግ መጽሃፍት ከተጻፉት ያልተፈጸመው ይሄ ብቻ
አይደለም ብዙ አሉ። ያ ማለት ህግ እስካሁን ይሰራል ማለት አይደለም
ኢየሱስ አቁሞታል።እንዴት? ብትሉ መጽሐፍ ፦ የሚያምኑ ሁሉ ይጸድቁ
ዘንድ ክርስቶስ የሕግ ፍጻሜ (the end of the law)ነውና። ሮሜ
10፥4 በማለት ተናግሯል። ህግ እንዴት እንደቆመ ወይንም እንደተሻረ
ከታች በስፋት እናወራለን።ከነብያት ደግሞ ያልተፈፀሙ ብዙ ትንቢቶች
ደግሞ አሉ። ሮሜ 11 (አዲሱ መ.ት) 26 ስለዚህ እስራኤል ሁሉ ይድናሉ፤
እንዲህ ተብሎ እንደ ተጻፈ፤ አዳኝ ከጽዮን ይወጣል፤ ከያዕቆብም
ክፋትን ያስወግዳል።፹ ኀጢአታቸውንም ሳስወግድ፣ ከእነርሱ ጋር
የምገባው ኪዳኔ ይህ ነው። የዚህ ትንቢት ፍፃሜ የሚሆነው ኢየሱስ
በታላቅ ክብር ዳግመኛ ሲገለጥ የሚሆን ነው። እንደዚህ የመሳሰሉት
ፍጻሜን ያላገኙ ብዙ ህግ እና ትንቢቶች አሉ።

# 2

# የህግ መሻር

## *ኢየሱስ ህግን ልሽር አልመጣሁም ያለው እና ጳውሎስ ህግ ተሽሯል የለበት መንገድ አንድ ነው?*

በፍጹም! በፍጹም! በፍጹም! ኢየሱስ በምድር ሳለ ሙሴ እንደዚህ ብሎ ነበር እኔ ግን እንደዚህ እላለሁ ብሎ ሲናገር ስለነበረ ኢየሱስ በራሱ ህግን የሻረ /የሰረዘ ይመስላቸዋል።ኾ.... ታዲያ ኢየሱስ" ህግን ልሽር አልመጣሁም "ሲል ለምን? ጳውሎስ "ህግ ተሽሯል" ይላል ትሉ ይሆናል። አዎ!, ኢየሱስ ልፈጽም እንጂ ልሽር ያለውን ልክ እንደሆነ ከላይ ተመልክተናል ስለዚህ በጌታም ተፈጽመዋል እንጂ አልተሰረዙም።በሌላ በኩል ደግሞ ሐዋርያው ጳውሎስ በጻፋቸው እና ሌሎች ሐዋርያት በጻፏቸው መልእክቶች ውስጥ ስለ ህግ መሻር የሚናገረውን ከዚህ ቀጥሎ እንመለከታለን። ሐዋርያው ጳውሎ የተናገረበትን አውድ እስቲ እንመልከት፦እግዚአብሔር የቀድሞውን ኪዳን ሽሮ ሌላ አዲስ ኪዳን እንዲያደርግ ያስገደደው ብዙ ምክንያቶች ቢኖሩት ከብዙ ጥቂቱን እንመለከታለን። በመጀመሪያ የዕብራውያን ጸሐፊ ከጻፈው እንጀምር ዕብራውያን ዕብራውያን 7

### [11] እንግዲህ ህዝቡ በሌዊ ክህነት የተመሠረተን ሕግ

**ተቀብለዋልና በዚያ ክህነት ፍጹምነት የተገኘ ቢሆን፥ እንደ አሮን ሹመት የማይቈጠር፥ እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ግን የሆነ ሌላ ካህን ሊነሳ ወደፊት ስለ ምን ያስፈልጋል?[12] ክህነቱ ሲለወጥ፥ ሕጉ ደግሞ ሊለወጥ የግድ ነውና።ቺይህ ነገር የተነገረለት እርሱ በሌላ ወገን ተካፍሎአልና፥ ከዚያም መሠዊያውን ያገለገለ ማንም የለም፤ኀ ጌታችን ከይሁዳ ነገድ እንደወጣ የተገለጠ ነውና፥ ስለዚህም ነገድ ሙሴ ምንም እንኳ ስለ ክህነት አልተናገረም።ኀ-[16] በማያልፍም ሕይወት ኃይል እንጂ በሥጋ ትእዛዝ ሕግ ሳይሆን ሌላ ካህን በመልከ ጼዴቅ ምሳሌ ቢነሳ፥ ይህ እጅግ አብልጦ የሚገለጥ ነው።ኀ አንተ እንደ መልከ ጼዴቅ ሹመት ለዘላለም ካህን ነህ ብሎ ይመሰክራልና።ኀ-[19] ሕጉ ምንም ፍጹም አላደረገምና ፥ ስለዚህም የምትደክም የማትጠቅምም ስለሆነች የቀደመች ትእዛዝ ተሽራለች ፥ ወደ እግዚአብሔርም የምንቀርብበት የሚሻል ተስፋ ገብቶአል።**

የዕብራውያን ጸሐፊ ክህነቱ ከአሮን በልጦ እንደ መልከጼዴቅ በሆነ ሹመት ስለሚሾመው ስለ ኢየሱስ የተናገረው እግዚአብሔር በቀድሞው በአሮን ክህነት ውስጥ ብዙ ችግሮች እንደነበሩት ስለተረዳ ነው።ምክንያቱም በዚያ ክህነት የሚሞቱ ሰዎች የሚያገለግሉ ስለሆነ፤ በነሱም ድካም ስለነበረባቸው እግዚአብሔር እራሱ አዲስን ኪደን ማድረግ ነበረበት፤ ጌታ ኢየሱስ የማይሞትና ዘላለማዊ ፍጹምም ስለነበረ እሱን የአዲስ ኪዳን ሊቀካህን አደረገው።

መጽሐፍ በዚሁ ስፍራ እንደሚናገረው " [12] ክህነቱ ሲለወጥ፥ ሕጉ ደግሞ

ሊለወጥ የግድ ነውና።"አስተውሉ!!! "ህጉ ስለ ተለወጠ ክህነቱ ሊለወጥ ግድ ነው" ሳይሆን ያለው "ክህነቱ ስለ ተለወጠ ህጉም ሊለወጥ ግድ ነው። "ነው ያለው። ስለዚህ ህጉ እንዲሻር ወይም እንዲለወጥ ግድ ያለው የክህነት ስርዐት በአዲስ ኪዳን ስለተለወጠ ነው። ከቀድሞው የተሻለ ወደ እግዚአብሔር የምንቀርብበት መንገድ አሁን ስለተገለጠ ነው። ሰው ወደ እግዚአብሔር የሚቀርብበት መንገድ ደግሞ የክህነት ስርአት ነው።ይህ የተሻለው መንገድ ምን እንደሆነ በሁለቱ ኪዳናት ያለውን ልዩነት በማነፃፀር እንዲህ ነው ፦

| | **በብሉይ ኪዳን** | **በአዲስ ኪዳን** |
|---|---|---|
| ❖ መስዋእቱ | በግ | ሰው(ኢየሱስ ) |
| ❖ ካህናቱ | ሚሞቱ | የማይሞት |
| ❖ የማስተሰረይ አቅም | አንድ አመት | ለዘለዓለም |
| ❖ መቅደሱ | ምድራዊ | ሰማያዊ |

የአሁኑ መንገድ አዲስ እንዲሆን የቀድሞው መንገድ መሻር ስላለበት ነዉ። የቀደመው ኪዳን ካህና ማለትም አሮንና ልጆቹ ሲሾሙ ያለ መሀላ ነበር ነገር ግን የአዲሱን ኪዳን ሊቀ ካህናት የሆነውን ኢየሱስን" አንተ እንደ መልከፀዴቅ ለዘላለም ካህን ነህ" በማለት በመሀላ እግዚአብሔር አጽድቆታል።በዚህም በማይለወጥና ዘላለማዊ በሆነ ክህነት እግዚአብሔር ሹሞታል፤ ከዚህም በኋላ ያለው የክህነት ስርአት አይለወጥም ፤ምክንያቱም ፍፁምና ዘላለማዊ ሆኖ በሰማያዊቷ ድንኳን እውነተኛ አገልጋይ(ካህን) ሆኖ ለተቤዣቸው በአባቱ ፊት ይታይላቸዋልና።

በቁጥር 18 ላይ ደግሞ"ሕጉ ምንም ፍጹም አላደረገምና፥ ስለዚህም የምትደክም የማትጠቅምም ስለሆነች የቀደመች ትእዛዝ ተሽራለች" ብሎ ይናገራል ስለዚህ እግዚአብሔር እራሱ ሰውን ፍጹም ለመድረግ የሚያስችል የክህነት ስርዓት ስላልሆነ ክህነቱን ዘላለማዊና ፍጹም ለማድረግ በአዲሱ ሻረው። የፊተኛውንና በማስረጃት አሮጌ ብሎታል።

በተጨማሪም ህጉ እንዲሻር ምክንያት ከሆኑት መካከል ህጉ እግዚአብሔርን ከእስራኤል የእስራኤልንም ከአህዛብ የለየ **የጥል ግርግዳ** ስለሆነ ነው። እግዚአብሔር በአብርሃም በኩል "የምድር አህዛብ በአንተ ይባረካሉ" ያለውን የተስፋ ቃል ለመፈጸም፤ የሚያምን ሁሉ እንዲድንና ያመኑቱ ሁሉ በክርስቶስ በኩል የአብርሃምን በረከት እንዲደርሳቸው ክርስቶስ የህግ ፍፃሜ (መጨረሻ) ሆኗል። ከአይሁድ የሚለየውን የጥል ግርግዳ የሆነውን ህግ በመስቀሉ ሽሯል ሕግንም፣ ከትእዛዛቱና ከሥርዐቱ ጋር በሥጋው **ሻረ**…." ስለሚል።

በመጨረሻም እግዚአብሔር የሙሴን ህግ እንዲሽር ምክንያቱ በመጽሐፍ በግልፅ የተቀመጡ ህጉን እንዲያመለክቱ የተጻፉ አሉ እነሱም ህጉ እንደጥላና ሞግዚት መጠቀሱ ነው። ሁለቱን በስፋት እንመልከት።

## ህጉ እንደጥላ ማገልገሉ

በመጽሐፍ ተገልጿል ከተባሉ የህጉ ባህሪያት አንዱ የሆነው ለክርስቶስ ኢየሱስ **ጥላ** መሆኑ ጥላ የሆነለት አካል በተገለጠ ጊዜ እንደሚሻር ማሳያል ይሆናል ። መጽሐፍ ስለዚህ ሲናገር ሕጉ ሊመጣ ያለው የበጎ

ነገር እውነተኛ አምሳል ሳይሆን የነገር ጥላ አለውና፥... ”ዕብራውያን 10፥1 ጳውሎስ በሌላ ስፍራ ደግሞ- ቆላስይስ 2

**16 እንግዲህ በመብል ወይም በመጠጥ ወይም ስለ በዓል ወይም ስለ ወር መባቻ ወይም ስለ ሰንበት ማንም አይፍረድባችሁ፤ኀ እነዚህ ሊመጡ ያሉት ነገሮች ጥላ ናቸውና፥ አካሉ ግን የክርስቶስ ነው።ኀ ትሕትናንና የመላእክትን አምልኮ እየወደደ፥ ባላየውም ያለ ፈቃድ እየገባ፥ በሥጋዊም አእምሮ በከንቱ እየታበየ ማንም አይፍረድባችሁ።ኀ እንደዚህ ያለ ሰው ራስ ወደሚሆነው አይጠጋም፥ ከእርሱም አካል ሁሉ በጅማትና በማሰሪያ ምግብን እየተቀበለ እየተጋጠመም፥ እግዚአብሔር በሚሰጠው ማደግ ያድጋል።፹-21 ከዓለማዊ ከመጀመሪያ ትምህርት ርቃችሁ ከክርስቶስ ጋር ከሞታችሁ፥፹፩ እንደ ሰው ሥርዓትና ትምህርት። አትያዝ፥ አትቅመስ፥ አትንካ ለሚሉት ትእዛዛት በዓለም እንደምትኖሩ ስለ ምን ትገዛላችሁ? እነዚህ ሁሉ በመደረግ ሊጠፉ ተወስነዋልና።፹፪ ይህ እንደ ገዛ ፈቃድህ በማምለክና በትሕትና ሥጋንም በመጨቆን ጥበብ ያለው ይመስላል፥ ነገር ግን ሥጋ ያለ ልክ እንዳይጠግብ ለመከልከል ምንም አይጠቅምም።**

ሐዋሪያው ጳውሎስ በዚህ ስፍራ በክርስቶስ ላመኑት ክርስቲያኖች። በአንደኛው ክፍለ ዘመን በክርስቶስ ያመኑ አይሁድ ያመኑትን አህዛብ ከዳኑ በኋላም እንኳን አይሁድ በሙሴ ህግ ያለውን እለትን፣ ወራትን፣ አመታትን ፣ጭምር እየጠበቁ ስለሚያከናውናቸው በአላትና ሰለመብልና

ሰለመጠጥ ያለውን ሳይፈጽሙ ሲቀሩ ከነሱ ሰለሚመጣለቸው ክስ ተቃርኖ ነበር ሚጽፈው። ምክንያቱም እንዚህ በሙሴም መጽሐፍ ያሉ ስለክርስቶስም የተጻፉ ፤"በመደረግ ሊጠፉ" ማለትም እስከ ክርስቶስ መገለጥ ድረስ እስራኤል ስርአቱን በማድረግ ወይም በመፈጸም ብቻ እንዲጠብቁ የተወሰኑ ናቸውና።

የዕብራውያን ጸሐፊ ደግሞ እግዚአብሔርን ላስደስት በሚል ወደነዚሁ ስርዓቶች ሊመለሱ ለነበሩ ዕብራውያን ከሙት ሥራ ስለመመለስ ወይንም ንስሐ የተናገረበት ስፍራ ነበር። ይሄ "የሞተ ስራ" የሚባሉት ሰው ደግም ከተወለደ በኋላ ቢሰራ ባይሰራ በእግዚአብሔር ፋት ምንም ለውጥ የማይኖራቸው፤ ልክ አንደ በአላትን፣ የወር በመባቻዎችን፣ ሰንበትን፣የተለያዩ ስርአትን መጠበቅ ማለት ነው። በአላትን፣ ሰንበትን፣የተለያዩ ስርአትን በመጠበቅ በክርስቶስ ኢየሱስ መገለጥ መሻራቸውን ባለማወቅ ፣በክርስቶስ አምነው የዳኑ አይሁድ አህዛብ ስርአቶቹን ባለመፈፀማቸው ኃጢያት እንደሰሩ የሚያስቡ፤ አይሁ ደግሞ ህሊናቸውን በዚሁ ሥራ ሊያነፁ የሚሞክሩ አሉ። ነገር ግን እነዚህ ስርአቶች ከህሊናችን ሊያየፁን አይችሉም ፤በክርስቶስ ደም እንጂ። ለዚህ ነው መጽሐፍ  በዘላለም መንፈስ አማካይነት ራሱን ነውር አልባ መሥዋዕት አድርጎ ለእግዚአብሔር ያቀረበው የክርስቶስ ደም ሕያው እግዚአብሔርን እንድናመልክ ኅሊናችንን ከምውት ሥራ እንዴት ይበልጥ ያነጻ ይሆን!”

ህግ ጥላ ሆኖ ማገልገሉን ስናጠቃልል ከላይ እንደ ተጠቀሰው መጸሐፍ እንዲህ ይላል ፦ሚያምኑ ሁሉ ይጸድቁ ዘንድ ክርስቶስ የሕግ ፍጻሜ (the end of the law,not the  fulfillment)ነውና ይላል፤ስለዚህ ህግና የህግ ዘመን መቋጫንና ፍፃሜን በክርስቶስ አግኝተዋል ።

## ህጉ ሞግዚት ሆኖ ማገልገሉ

እግዚአብሔር ለአብርሃም በዘሩ(በክርስቶስ) በኩል ለአህዛብ የሚደርሰው በረከት እስኪመጣ ድረስ በመካከል የገባ የአብርሃምን ኪዳን መሻር በማይችል መልኩ ልክ ልጅ እናት አስክትመጣ ድረስ ለሞግዚት እንደሚሰጥ እንደዛው ህግ እስራኤልን ፀጋ(እምነት) እስኪገለጥ ድረስ የጠበቀ ነው እንዲህ ስለሚል- ገላትያ 3 ፡-ቹ እንደዚህ በእምነት እንጸድቅ ዘንድ ሕግ ወደ ክርስቶስ የሚያመጣ ሞግዚታችን ሆኖአል፤ ቹ እምነት ግን መጥቶአልና ከእንግዲህ ወዲህ ከሞግዚት በታች አይደለንም። ስለዚህ በነዚህ ሁሉ ምክንያቶች ህግ እንዲሻር ምክንያት ሆኗል።በነገራችን ላይ ህግ በነበረበት ዘመን ሰዎቹ ህጉን ሲጥሱ ከተገኙ ያለርህራሄ ይገደላሉ ምክያቱም እግዚአብሔር ሰዎቹን ስለሚጠላ ሳይሆን ሞግዚት ለልጆች የሚያስብ የእናት (የፀጋ) ልብ ስለሌላት ልጆችን ዝም ብላ ትቀጣለች።ስለዚህ በብሉይ ኪዳን የብዙ ሰዎች ይሞታሉ ይቀሰፋሉ። እግዚአብሔር ፍቅር ስላልሆነ ሳይሆን እግዚአብሔር የሚያደርግላቸውን ነገር በህጉ መዝኖ እንዲያደርግ በመፈለግና በመተላለፍ ምክንያት የተሰጠ ሞግዚት ስለሆነ ምህረትን አያውቅም።እግዚአብሔርም ቸርነቱን እንዲገልጥ እድልን አይሰጥም ነበር አሁን ግን እንደዛ አይደለም ክርስቶስ በመስቀሉ ህግን ሽሯልና።ሃሌሉያ!!

### "ኢየሱስ የህግ ዘመን ፍፃሜ የጸጋ ዘመን ጅማሬ ነው።"

ክርስቶስ የኢየሱስ ካረገ በኋላ የገዛ ወገኖች የሆኑት እስራኤላውያን ስላልተቀበሉት እግዚአብሔር እስራኤልን ሊያስቀና ፈልጎ ፊቱን ወደ አህዛብ አዙሯል እንዲህ በማለት፡-ሮሜ 10 ፡-ጎ ሙሴ አስቀድሞ ፡-እኔ

ሕዝብ በማይሆነው አስቀናችኋለቸሁ በማያስተውልም ሕዝብ አስቆጣችኋለሁ ብሎአል።

20 ኢሳይያስም ደፍሮ፦ ላልፈለጉኝ ተገኘሁ፥ ላልጠየቁኝም ተገለጥሁ አለ።እግዚአብሔር በንዲህ አይነት ትንቢት ከእስራኤላውያን ለጥቂት ጊዜ ፊቱን ወደ አህዛብ እንደሚያዞር ፤ይህም ጥቂት ጊዜ የፀጋ /አህዛብ ዘመን እንደሚሆን በተናግሯል።

# 3

# ህግን ማድረግ

አንድ እስራኤላዊ ህይወቱን መምራት ያለበት በሙሴ ህግ እንደሆነ ይታወቃል ነገር ግን ሙሴ ካዘዛቸው ትዕዛዛት አንዷን እንኳን ባያደርግ ኃጢያተኛ እና በደለኛ እንደሆነ ይቆጠራል ስለሆነም ለኃጢአቱ ማስተሰርያ ይሆን ዘንድ በግ ያመጣ ነበር።

## *ኢየሱስ በሰንበት በመፈወሱ ህግን ተላልፏል ወይ?*

ኢየሱስ በምድር ሲመላለስ እንደ አንድ እስራኤላዊ ሲያገለግልም ሆነ ድንቆችን ሲያደርግ በሰንበት የታምራትን ሲፈጽም ለምን ሰንበትን እና የሙሉን ህግ ትሽራለህ ይሉት ነበር።እውነታው ግን ኢየሱስ ከሙሴ ህግ አንዷቷን እንኳን አልተላለፈም ነገር ግን ይጠብቅና ያደርግ ነበር ይህ ባይሆን ኖሮ አዳኛችን ባልሆነ ነበር።ምክንያቱም የትኛውም እስራኤላዊ ስለ ኃጢያቱ እንዲቤዠው ወይንም ምትክ ሆኖ በእርሱ ቦታ የመስዋዕት በግ እንዲሆን ሲያቀርብ በጉ ንፁህ እና ነውር አልባ መሆን አለበት።አስቲ ጸሐፍትና ፈሪሳዊያን ኢየሱስን ሰንበትን ለምን ትጥሳለህ በሚል ይከሱንና ኢየሱስ ስላለመተላለፉ የመለሳቸውን መልሶችን እንመልከት ፦ዮሐንስ 7 [21] ኢየሱስ መለሰ አላቸውም፦ አንድ ሥራ አደረግሁ ሁላችሁም ታደንቃላችሁ። ፳፪ ስለዚህ ሙሴ መገረዝን

ሰጣችሁ፤ ከአባቶችም ነው እንጂ ከሙሴ አይደለም፤ በሰንበትም ሰውን ትገርዛላችሁ።

[23] የሙሴ ሕግ እንዳይሻር ሰው በሰንበት መገረዝን የሚቀበል ከሆነስ ሰውን ሁለንተናውን በሰንበት ጤናማ ስላደረግሁ ትቈጡኛላችሁን? ይህ የግርዘት ህግ የመጣው ከአባቶች ነው። ፦የትኛውም እስራኤላዊ ወንድ ህፃን በተወለደ በስምንተኛው ቀን የመገረዝ ግዴታ አለበት ፤ይህ ስምንተኛ ቀን ሰንበትም ቢሆንም ወደ ቤተመቅደስ መጥቶ መገረዝ አለበት። ለዚህ ነው ኢየሱስ ሙሴ በሰንበት መገረዝን ከፈቀደ ወይንም የሰውን የሆነ አካሉን ማንፃትን ከፈቀደ እኔ የሰውን ሁለንተና ባነፃ ወይንም ብፈውስ አይከለክልም በማለት ለህግ ተቆርቋሪ ነኝ ባዮች ሙሴ ስለዚህ ነገር የተናገረውን ተረጎመላቸው። እንደውም የአንድ አይሁዳዊ ህጻን ግርዘቱን የሚፈጽምበት ቀን ሰንበት ሆኖ የቤተሰቡ ቤት ምንአልባት ከእየሩሳሌም ሩቅ ቢሆን ይህ ቤተሰብ የህጉን ስርአት ለመፈፀም በሰንበት ቀን እንዲጓዙ ከተፈቀደላቸው በላይ ይራመደሉ ማለት ነዉ። በተመሳሳይ ጌታ ኢየሱስ ረዥም ርቀት በመሄድና በተለያዩ ከተሞች በመዟዟር ያገለግል ስለነር ህግን በመተላለፍ ይከሱት ነበር።

ሌላኛው ደግሞ ኢየሱስና ደቀመዝሙርቱ በሰንበት በሰው እርሻ እሸት ቀጥፈው ሲበሉ ፈሪሳውያን አይተው ለምንድነው" በሰንበት ሊደረግ ያልተፈቀደውን ነገር የምታደርጉት" ብለውት ጠየቁት ኢየሱስም እንዲህ ብሎ መልሶ ነበር ካህናት በቤተ መቅደስ በሰንበት ቀን ቢያገለግሉ ኃጢያት እንደማይሆንባቸው ወይንም ህግን ተላልፋችዋል ተብለው እንደማይከሰሱ አታውቁምን? በማለት ካህናት የእግዚአብሔር አገልጋይ እንደሆኑ ሁሉ እንዲሁም ጌታ ኢየሱስ እና የእሱ ደቀመዛሙርትም አገልጋዮች ስለሆኑ በሰንበት ማገልገል በሙሴ እንደተፈቀደ ህግ ጠቅሶ ህግን እንዳልተላለፈ አስረድቷል።አያችሁ!! ኢየሱስ በህጉ ውስጥ

ያለውን፤ እነሱ ግን ሊረዱ ያልቻሉትን በግልጥ በማስረዳት ይነግራቸዋል። ከዚህም የተነሳ ክርስቶስ ኢየሱስ ህግ እየተላለፈ እንዳልሆነ ግን እየጠበቀና እያደረገ እንደሆነ እንረዳለን። ጴጥሮስም "እሱ ኃጢያትን አላደረገም በአፉም ተንኮል አልተገኘበትም" በማለት በድርጊት ኃጢያት እንዳልሰራ አረጋግጧል። ስለዚህ እሱ አዳኝኛችንና ቤዛችን ሆኗል። ስለዚህ የእነዚህ ኀሳቦች ድምዳሜ ኢየሱስ በተናገረበት አውድ ኢየሱስ ህግን አልሻም ፤ ሐዋርያቱ በተናገረበት አውድ ደግሞ ተሽሯል ፤በነገር ሁሉ እኛን በመምሰል ህግን በመጠበቅና በማድረግ ተመላልሷል።

**"ጌታ ኢየሱስ እንደ እስራኤላዊ ህግን በማድረግ፤ እንደ አካል በመሻር ፤እንደ መሲህ በመፈጸም በምድር ተመላልሷል።"**

## *ዋቢ መጽሐፍት / Bibliography*

❖ አማርኛ መጽሐፍ ቅዱስ 1954 ዓ.ም
❖ አዲሱ መደበኛ ትርጉም (አ.መ.ት)